# የዕርቅ ሐወልት ብንተክልስ?

ባገራችን ምድር የተሻለ ስርዓት ለመትከል በመስራት ላይ ነን የሚሉ ሃይሎች ወይም የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ያነገቡትን አላምና መርህ የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ ነው ለማለት ይከብዳል። በተግባር አብዛኛዎቹ የግል ጉዳይና ጥቅም እንዲሁም ዝና የሚገዳቸው ናቸው ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም። ለዚሁ ነው ተቃዋሚ ወገን የረባ ነገር እስካሁንዋ ደቂቃ ለመስራት ያልቻለው። እያንዳንዱ ድርጅት የራሱን አጥር በማበጀት በጋራ ለጋራ የሚለው ዋነኛው የትግል መርህ ወደ ጎን በመግፋትና ቢታሰብም ተግባራዊ እንዳይሆን እየተጉ መሆናቸውን ግንዛቤ የጎደላቸው ይመስላል።

**ተጨባጩ ምንድነው?**

ኢትዮጵያ አገራችን ከደርግ ስርዓት ጀምሮ እስከ አሁን የሄደችው ጉዞ ብንመረምር እጅግ የተወሳሰበ ሁኖ እናገኛዋለን። ከዚሁ ዋንኛውና ትልቁ የምለው ደግሞ በምሁሩ መሃል የበቀለው ቂምና ቁርሾ ነው። ባንድ ወቅት በጥሩ ልቦና ላገሬ የተሻለ ስርዓት አመጣለሁ ብሎ በየጎራው ተሰልፎ የታገለው ወገን ሳያውቀው ወደ እርስ ብርስ ሽኩቻና ትንቅንቅ በማምራቱ በመሃል የብዙ ሺ ኢትዮጵያውያን ህይወት በከንቱ እንዲያልፍ ምክንያት ሁነዋል። እንግዲህ አሁን ላለው አለመግባባት መሰረት የጣለው ያ ያበደ ግዜ ነበር ለማለት ይቻላል። ይህንኑ አሳፋሪ በደል የፈፀሙ ደግሞ ከሌላ ዓለም የመጡ ሳይሆኑ የራሳችን ወገኖችና ኢትዮጵያውያን ብለን የምንጠራቸው ናቸው። ይህንኑ አስነዋሪ ድርጊት ሲፈፅሙና ሲያስፈፅሙ ደግሞ የማያውቁትን ርዕዮተ አለም ሰንቀውና የባዕድ ፍልስፍና ታጥቀው እንደነበረ ሁሉም ወገን የሚያውቀው ነው። እና በህዝባችን፣ በታሪካችንና፣ ባንድነታችን ለተፈጸመው ወንጀል መሰረቱ ያ ነበር ለማለት ይቻላል። እንግዲህ ያንድ ወቅት ታሪካችን ይህኑን ከመሰለ፣ መፍትሄው ስንፈልግ ደግሞ ያንን የፈጠረውን የህሊና ቁስል ለመፈወስ የሚረዳ መሆን እንዳለበት የግድ ይላል።

**መፍትሄውስ?**

ስርዓትን በመቀየር ያልተፈታው ችግራችን እንግዲህ **ቁልፉ ወይም መፍትሄ ስራዩ ዕርቅ** ነው። ከዚሁ ውጭ ሌላ አማራጭ ያለን አይመስለኝም። የተሰበረና ያዘነ ልብ ከዕርቅ ውጭ ሌላ ሲፈውሰው በህይወቴ አላየሁም። ከዕርቅ በሃላ ያ ሁሌ የምንመኘው እድገትና ብልጽግና ለማምጣት ብዙ የሚያስቸግር አይመስለኝም ምክንያቱም የዚሁ ሁሉ መሰረት ንፁህ/ጥሩ ልብ ስለሆነ። ሌላውይቅር፣ ይቅር ከተባባልን በሃላ ለዚሁ ታሪካዊ ፍጻሜ ማስታወሻ እንዲሆነን የእርቅ ሃወልት ብንሰራስ ምንኑ ያስከፋል? ይህ ቅዱስ ተግባር እስከ ዳር ለማድረስና ለመተግበር ደግሞ የልብ ቅንነትና ትልቅነት እንጂ የትምህርት ሊቅነት ለብቻው የትም አያደርስም። እና **ማን ይሆን ትልቅ ሰው?** የሚለው የአለማየሁ እሸቴ ዘፈን ላለንበት ወቅት በተለይ ትልቅ መልዕክት ያለው ይመስላል። አሁን ከምናየው የጥቅምና የዝና ፍኖት ራሱ ያገለለ፣ ሰላምና ፍቅር እንዲሁም ዕድገት ባገራችን ለማስፈን ፍላጎት ያለው ወገን ወደ መድረክ ብቅ እንዲል አምላክ በኪነ ጥበቡ እንዲያግዘን የዘወትር ልመናችን ነው።

በደርግ፣ በኢ. ሕ አ ፓ፣ በወያኔ እንዲሁም በሌሎች ጎራ የተሰለፈው ወገን እናት አገሬ ይህንኑ ነው የሚበጃት ብሎ የተሰለፈ ነበር እንጂ ጥቅምና ሹመት አገኛለሁ ብሎ አልነበረም። እና ማንም ለማንም ያንተ የተሳሳተ አመለካከት ነበር የኔው ግን ትክክል

ነው የሚያስብል ሞራልና ብቃት ያለው ድርጅት ወይም ግለሰብ ያለ አይመስለኝም። ሁሉም ባመነበት ተሰለፈ፣ የሚመስለው ተግባርም ፈጸመ። እንዲያ ሁኖ ግን ያ ያንድ ወቅት ስህተትና ጥፋት እኛን እያለያየና እያባላን እንዲኖር መፍቀድ የለብንም። የተከፋፈለች ቤት ለራስዋ መቆም አትችልም የሚለው የክርስቶስ ብሂል ምን ያህል እውነት መሆኑን በውል የምንገነዘብበት ወቅቱ አሁን ነው።

እንደሚታወቀው ታሪክ በጣም ንፉግ በመሆኑ ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ ጥሩ ነገር ሰርተው እንዲያልፉ እድል ይሰጣል።ሁሌም ታሪክ የሚሰራው ደግሞ በቆራጦችና በውህዳን ነው። እና ታዋቂ ግለሰቦችና ባንድ ወቅት በሃላፊነት ደረጃ የነበሩ ወገኖች አሁን ካለው የፖለቲካ መናቆር ወጥተው አገርና ህዝብ ለዘላለም በሚያስታውሰው ማለትም <u>በማስታረቅ</u> ስራ ቢሰማሩ የበለጠ ይሳካላቸዋል ብዬ አምናለሁ። መንግስትንና ተቃዋሚ ወገን ተቻችለው ላገር እንዲሰሩ ማስቻል ማለት ትርጉሙና ጥቅሙ ወደር የለውም።

ላገር ቤዛ መሆን ወቅቱ አሁን ነውና ይህንኑ ቅዱስ ስራ እንዲፈጽሙና አምላክ እንዲያግዛቸው ምኞቴ ከፍ ያለ ነው።

ሰላምና ፍቅር እንዲሁም ብልጽግና ለኢትዮጵያ ይሁን!
አሜን!

ሃይለ ደስታ